# የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጪ ዜጎች
# በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች
# ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ
# የማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 18 /2006

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Foreign Affairs

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

## መግቢያ

የኢፌድሪ መንግስት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ሀገር ዜጐች ከትውልድ ሀገራወቸው ጋር ትስስር ኖሮአቸው በአገራቸው ልማት ተሳታፊ በመሆን አገራቸውን ጠቅመው ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ በአገር ውስጥ አመቺ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ አዋጅ ቁጥር 270/94፣ አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንብ ቁጥር 2252/2003 ደንብ ቁጥር 101/2004 እንዲሁም ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የማስፈፀሚያ መመሪያች ወጥተው ለተወላጁ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ አገልግሎት በሀገር ውስጥ በኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ እና በውጪ ሀገር በኢፌድሪ ሚሲዮኖች ሲሰጥ እንደነበር ይታወቃል፡፡

በዚህ መሠረት አያሌ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ አገልግሎት አግኝተው በሀገራቸው ልማት እየተሳተፉ የሚገኙ ሲሆን በአገር ቤት ቆይታቸው ወቅትም ህጉ በሰጣቸው መብቶች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ተወላጁ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በየጊዜው የተለያዩ ጥያቄዎች ለማንሳት ቅሬታ እያሰማ በመሆኑ፣ የእስከአሁኑ አሰራር የህጉን አላማ ለማስፈጸም ባለማስቻሉ እና ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች መመሪያውን በዚህ መንፈስ በማሻሻል መፍታት አስፈልጓል፡፡

1. **መመሪያውን ማሻሻል ያስፈለገበት አብይ ምክንያቶች**
   - በሀገር ውስጥና በውጭ አገር በመታወቂያ አገለግሎት አሰጣጥ ረገድ የነበረው አሠራር ወጥነት የሌለው መሆን፣
   - ከሚሲዮን ሚሲዬን በመታወቂያ አገልግሎት አሰጣጥ የነበረው አፈፃፀም የተለያየና አንዳንድ ጊዜ በሚሲዬን መሪያዎችና አገልግሎቱን በሚሰጠው ዲፕሎማት መልካም ፈቃድ ላይ የተመሠረተ መሆን፣
   - አገልግሎቱን ለመስጠት በመመሪያው የተቀመጡት አንዳንድ መሥፈርቶች በተለይ በማስረጃ አቀራረብ በተጨባጭ ሲታይ ሊተገበሩ የማይችሉ ሆነው መገኘት፣
   - በመታወቂያ ካርድ አሰጣጥ የተጠያቂነት አሠራር አለመኖር፣

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs